ርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
Re'ese Adbarat Debre Selam Kidest Mariam
Ethiopian Orthodox Tewahido Church

*"እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፤ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁአቸው የአኔ ደቀመዝሙር አድርጓቸው "። ማቴ ፳፰፣ ፲፱*

*"Therefore go and make disciples of all nations, baptizing them in the name of the Father and of the Son and of the Holy Spirit, "Matthew 28:19*

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::

ሚያዚያ ፲፫ ቀን ፳፻፯ዓም/ April 21 2015

**በ፳፩ኛው ክፍለ ዘመን**

**፴ ሰማዕታተ ኢትዮጵያ**

**በዓለም ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሙሉ**

**የመሪር ኃዘን መግለጫ**

**"ይህንንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፥ አያሌ ቀንም አዝን ነበር፤ በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር።" ነህምያ ፩፡-፬**

እኛ በዋሽንግተን ዲሲ የምንገኘ የርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ካህናትና ምዕመናን ሰሞኑን በየመን፣በደቡብ አፍሪካ በኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ባለው አሰቃቂ ሞት እያዘንን ባለንበት ወቅት አሁን ደግሞ በሊቢያ በISIS የተካሄደው አሰቃቂና በዚህ ዘመን የሰው ልጅ ከአውሬነት በባሰ አረመኒያዊ በሆነ መንገድ በ፴ ኢትዮጵያውያን ላይ በተፈጸመው የአንገት መቅላት ግድያ የተሰማንን መሪሪ ኃዘን ለመግለጽ እንወዳለን። እንዲሁም ለሰማዕታቱ ቤተሰቦች የሚያረጋጋና የሚያፅናና መንፈስ ልዑል እግዚአብሔር እንዲልክላቸው በጸሎታችን እንማፀናለን። **"በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።" ያዕቆብ ፩፡-፲፪**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለህዝቧ የማትመች የምድር ሲኦል በመሆኗ ወገኖቻችን የተሻለ ህይወት ፍለጋ ስደትን መፍትሔ አድርገው አውራ እንደአጣ ንብ በመቅበዝበዝ በዓለም መበተናችን የታሪካችን ክፍል ሆኗል። በተለይ በመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮችና በየመን በኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን የደረሰው ውርደትና ሰቆቃ የትላንት ትዝታችን ነው። እነሆ አሁን ደግሞ በአህጉራችን በአፍሪካ ቀደም ሲል በአገራችን በጅማ፣



1350 Buchanan St. NW, Washington, DC 20011
ስልክ/Tel: (202) 726 4115 ፋክስ/Fax: (202) 726 4056 www.dskmariam.org

በግብፅ፣በሶሪያ፣በደቡብ አፍሪካ የተፈጸመው በሊቢያ ተደገመ። በሊቢያ የተፈጸመው አሰቃቂ ግድያ በቃላት ለመግለጽ የሚያስቸግር የሚያሳዝንና ስቅ ብሎ የሚያስለቅስ መሪር ሀዘን ሆኖብናል። እነዚህ ሰማዕታት ወገኖቻችን ዓለምን እያወኩ ባሉ ጨካኝ አክራሪዎች ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው ብቻ  መስዋዕትነትን ተቀበሉ። ይህ የሚጠቁመው እምነታቸውን ስለአልቀየሩ መስዋዕትነትን የሚከፍሉ ዓለም ያላወቀው፣ የብዙኋን መገናኛ ያልዘገበው፣ በቁጥር ያልተገለጸ ስፍር ቊጥር የሌላቸው ወገኖቻችን ዕለት ዕለት እየተቀሉ እንዳሉ ነው።

በዚህ ክፉ ዘመን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን የአውሬና የአሣ ነባሪ ቀለብ ሆነው ሰቆቃቸውን የሚሰማ ማንም የላቸውም፣ ዓለም ጆሮ ዳባ ብላለች። እኛም ወገኖቻቸው ወደ ልባችን ተመልሰን ከውሸት፣ ከምቀኝነት፣ ከራስወዳድነት፣ ከፍቅረ ነዋይ  ወጥተን፤ በእምነታችን ፀንተን ለእውነት፣ ለፍቅር፣ ለአንድነት እንዳንገዛ ልባችን ደነደነ፤ በእኛ ልብ መደንደን ምክንያት ጸሎትና እንባችንን አይቶ አምላክ ኢትዮጵያን ከመከራዋና ከፍዳው በቃሽ ሊላት አልቻለም።

እንደ ጧት ጤዛ ለተወሰነ ጊዜ ታይቶ ለሚጠፋ ገንዘብ፣ እንደ ዝናም አልባ ደመና ተኖ እንዳልነበረ ለሚሆን ሹመትና ሽልማት፤ ፍርሐትና እራስወዳድነት ከሞት በአሻገር ያለውን ተስፋና ሰማያዊ መንግሥት አለ ብሎ  ባለማመን በሥጋ ሕይወት ደስታ ተጠምደን በምድር ብልጭልጭ ኑሮ ተታለን ለእውነቱ ዓለም ባዕድ ሆነናል።  ይህቺ ዓለማችን ፍጹም ሆና አታውቅም። ያለፍናቸው ዘመናት የተሻሉ የሚያደርጋቸው በሐሰተኛውና በእውነተኛው መካከል ያለው ቁጥር እኩል በኩል በመሆኑ ነበር። ዛሬ ግን እውነት ተናጋሪው ከአሥር እጅ አምስት ሊገኝ ቀርቶ ሁለት ሦስት ሊገኝ አይቻልም። ሐሰተኛው በዛ።የአብርሃም ዘመን ሆነ። ዛሬ የሰማዕትነት ሥራ ልንሠራ ይቅርና ሐውልታቸውን እንኳን ማትረፍ አልተቻለም። የተረከብናቸውን ታሪክና ቅርስ ፤ገዳማቱን እንደተረከብነው ለልጆቻችን ማስረከብ አልተቻለንም። የተለያየ የባዕድ እምነትና ፍልስፍና ገባ። የነበረው እምነታችን ተበከለ። ከተበታተነ የእምነት ምንጮች እየተጠጣ ትርፉ መበታተን ሆነ። መጠበቁ ቀርቶ መደማመጥ መስማማት አልቻልንም። ሁሉም  የኖኅ ዘመን



1350 Buchanan St. NW, Washington, DC 20011
ስልክ/Tel: (202) 726 4115   ፋክስ/Fax: (202) 726 4056   www.dskmariam.org

ሆነብን። ከህንፃ ሠናዖር ግንባታ ዘመን በከፋ ሁኔታ ላይ እንገኛለን። እነዚህ ፳፫ ወጣት ሰማዕታት ለማዕተባቸው፣ ለእምነታቸው መስዋዕትነትን ከፍለዋል። ሰማዕትነት የቆመለትን ዓላማ መርምሮ የመቃብር አድማስ የማይወስነውን በእውነት ጽድቅ መዝኖ ለተረዳት ለሰው ልጅ ክብር ለፈጣሪ ልዕልና እራስን ማቅረብ ነው።

እነዚህ የጽድቅ አርበኞች ሰማዕታት የሚገለጹትና የሚታዩት ዘመኑ ሲከፋ ነው። በሕዝቡ መካከል ለእውነት የሚቆም ከመቶ አምስት እንኳን በጠፋበት፣ ክፋትና ሐሰት በነገሠበት ዘመን፤ የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት መሪዎች በሐሰት ተስማምተው የኅብረተሰቡን (የሕዝቡን) ሃይማኖታዊውንና ማኅበራዊውን (መንፈሳዊውንና ዓለማዊውን) ሕይወት ሲያጨልሙበት ነው።እንዲሁም የሚውጥ የሰው ዘንዶ በተከሠተበት ጊዜና የቅዱሳንን መንፈስ የሚሰባብሩ አንበሶች ጅቦች ከጎሬያቸው ወጥተው በሕዝብ መካከል በተሰማሩበት ጊዜ፣ ቀኑ በጨለመበትና ሕይወት በደፈረሰበት ጊዜ ነው። እነዚህ ሮጠው ያልጠገቡ ወጣት ሰማዕታት በሞታቸው እኛን ቋሚዎቹን ለማስተማር ይኸው በዚህ ቀውጢ ዘመን በሰማዕትነት ብቅ አሉ።

ይህ ሁሉ የዘመኑ መከፋት ምልክት ነውና በመጨረሻም፤ውሸት አይሎ በእውነት ላይ ግርዶሽን ስለጣለ በእውነት በጨለማ ተውጣለች። አሁን የተያዘው እውነት ያለባቸውን ቦታዎች ማፍረስ ነው። የእውነትን ፋና በያዙት ሰዎች መዝመት ነው። እነዚህም ወጣት ሰማዕታት ለምን ተገደሉ? ስለምንስ ተሰው ብለን እራሳችንን እንጠይቅ! ደግመን ደጋግመን እራሳችንን እንጠይቅ!

የደረሰብን ኃዘን መሪር ነውና መጽናናቱን እንዲያድለን፤ ጠፍረው ከያዙን ከሐሰት፣ ከምቀኝነት፣ ከራስ ወዳድነት፣ ከፍቅረ ነዋይ፣ ከሥጋ ጥቅም ወዳድነት፣ ከአጉል አገዛዝና የሰብዓዊ መብቶች ከተረገጠበት ሁኔታ አውጥቶን ለእውነት የምንቆም ፅኑ ዜጎች ሆነን፣ ኢትዮጵያ ሀገራችንን ከገባችበት ማጥ የምናውጣ፣ ማጅራቷን አንቆ ከያዛት መጻጉእ የምናላቅቃት የእምነትና የእውነት አርበኞች እንዲያደርገን የአምላካችን መልካም ፈቃዱ ይሁንልን።



1350 Buchanan St. NW, Washington, DC 20011
ስልክ/Tel: (202) 726 4115 ፋክስ/Fax: (202) 726 4056 www.dskmariam.org

የተወደዳችሁ ወገኖቻችን፡- የደረሰብንና እየደረሰብን ያለው መከራና ሰቆቃ ከባድ ነው። የሃገራችንንና የቤተክርስቲያናችንን ትንሣኤ እንዲያሳየን በእምነታችን እንፀና፣ በተግባር እንበረታ ፣በጸሎታችን እንተጋ ዘንድ የአምላካችን ቅዱስ ፈቃድ ይሁንልን። **“በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤” ኤፌሶን ፮፡-፲፰**

ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በያላችሁበት ብርታትና መጽናናትን ያድላችሁ። በዚህ አጋጣሚ ይህንን ኢሰብዓዊ የሆነውን አሰቃቂ ድርጊት ወገኖቻችን በሙሉ በያላችሁበት፣ የዓለም ሕዝብ ሁሉ እንዲያወግዝ የሚቻላችሁን እንድታደርጉ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

እግዚአብሔር ሃገራችንን ኢትዮጵያንና ቤተክርስቲያናችንን ይጠብቅ።

የርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ዋሽንግተን ዲሲ



1350 Buchanan St. NW, Washington, DC 20011
ስልክ/Tel: (202) 726 4115 ፋክስ/Fax: (202) 726 4056 www.dskmariam.org